**የእግዚአብሔር መንግሥት በመኃልየ መኃልይ መጽሐፍ ውስጥ**

**ፍቅር፣ ታማኝነትና የመንግሥቱ ባሕል**

ዋና የንባብ ክፍል፡- መኃልየ መኃልይ 8፥6–7

**ዓላማ**፡- አማኞች በትዳርና በግንኙነታቸው ውስጥ የፍቅርን፣ የታማኝነትንና የቁርጠኝነትን እ ሴቶች በመኖር የእግዚአብሔርን ጽድቅና ቅድስና እንዲያንጸባርቁ ማበረታታት።

**ዋና መልእክት**፡- የመኃልየ መኃልይ መጸሐፍ በዋነኝነት ስለ ባልና ሚስት ፍቅር የሚናገር መጽ ሐፍ ቢሆንም፣ ከእግዚአብሔር መንግሥት አንጻር ስናጠናው **ፍቅር፣ ታማኝነት፣ ቅድስና እና የቃል ኪዳን ግንኙነት** በሕይወታችን ውስጥ ምን ያህል **አስፈላጊ** እንደሆኑ እንማራለን።ሆኖም መኃልየ መኃልይን ከመንግሥቱ አንጻር ስናብራራ፣ የመጽሐፉን ቀጥተኛ ትርጉም ማለትም በባ ልና በሚስት መካከል ያለውን የፍቅር ሀሳብ መጠበቅ አለብን። ከዚያም የመንግሥቱን መርሆ ች ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር በማያያዝ ማብራራት ይገባል።

**መግቢያ** ፡-የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ የሚገዛበትና ፈቃዱ የሚፈጸምበት የግዛት አገዛዝ ነው። የመንግሥቱ ባሕል በአማኞች አስተሳሰብ፣ በባሕርይ፣ በቤ ተሰብና በግንኙነቶቻቸው ውስጥ መታየት አለበት። መኃልየ መኃልይ **የፍቅርን ውበት፣ የግን ኙነትን ደስታና የታማኝነትን ክብር** የሚገልጽ መጽሐፍ ነው። ስለዚህ ከዚህ መጽሐፍ በመነሳ ት የእግዚአብሔር መንግሥት በፍቅራችንና በግንኙነታችን ውስጥ እንዴት መገለጥ እንዳለበት መማር እንችላለን ከዚህ እይታ አንጻር ሦስት ዋና ነጥቦችን እንመለከታለን።

**1፡በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ፍቅር የከበረ ስጦታ ነው**

መኃልየ መኃልይ 8፥6 **“ፍቅር እንደ ሞት ብርቱ ነው።”** እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረ በ ኋላ በግንኙነት እንዲኖር ፈቃዱ ነበር። **በዘፍጥረት 2፥18** ላይ፣ ሰው ብቻውን መኖሩ መል ካም እንዳልሆነ እግዚአብሔር ተናግሯል። ይህም በትዳር ውስጥ ያለው **የፍቅርና የአጋርነት ግንኙነት** በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ፍቅር ምን ያህል ቦታ እንዳለው ያሳያል።ከዚህ እውነት አንጻር ስንመለከተው መኃልየ መኃልይ የባልና የሚስትን ፍቅር እንደ ውብ፣ የተከበረና ጠንካራ ግ ንኙነት ያቀርባል። **ከመንግሥቱ አንጻር ደግሞ ይህ ፍቅር በራስ ወዳድነት ሳይሆን በክብር ፣ በመረዳዳትና በመተማመን መገለጥ እንዳለበት ያሳስብናል።**

**ግብረ መልስ** እንደ መንግስቱ ዜጎች ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው መከባበር አለባቸው።እንዲሁም ፍቅራችንን በቃል ብቻ ሳ ይሆን በተግባር መግለጽ አለብን። የመንግሥቱ ባሕል በቤተሰባችን ውስጥ መታየት አለበት።

1ኛቆሮ13፥4–
7።ምክንያቱም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ፍቅር የሚናገሩት ቃል ብቻ ሳይሆን፣ በባሕ ርያችንና በድርጊታችን የሚገለጥ ሕይወት ነውና።

**2 የመንግሥቱ ፍቅር ታማኝነትንና ቁርጠኝነትን ይጠይቃል**

መኃልየ መኃልይ 6፥3 **“እኔ የውዴ ነኝ፥ ውዴም የእኔ ነው።”** ይህ ጥቅስ በፍቅር ግንኙነት ውስጥ ያለውን የመተማመንና የመሰጠት ስሜት ያሳያል። እውነተኛ ፍቅር በስሜት ብቻ አይመ ሠረትም፤ነገር
ግን **በታማኝነት፣ በቁርጠኝነትና በተግባርም** ይገለጣል።የእግዚአብሔር መንግሥት የቃል ኪዳ ን ታማኝነትን ከፍ አድርጎ ያስተምራል። በትዳር ውስጥ ታማኝነት ማለት **በቃል፣ በሐሳብና በ ተግባር** ለትዳር
አጋራችን ታማኝ መሆን ነው። ይህን የታማኝነት መርህ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነትም ውስጥ አስፈላጊ እንድሆን በዚህ መጸሐፍ ውስጥ እንማራለን። እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ታማኝ ነው፤ እኛም ለእርሱ በእምነትና በታዛ ዥነት መኖር አለብን።

**ግብረ መልስ** በትዳር ውስጥ ታማኝነታችንን ጠብቅ። ቃል የገባኸውን ነገር በታማኝነት እንፈጽ ም።ከሰውች ጋር
ባለን ግንኙነት ውስጥ እውነተኛነትንና መተማመንን አጠናክር።በእግዚአብሔር ፊት የምትንናገ ረውና የምናደርገው ነገር አንድ እንዲሆን ጥረት አድርግ። ኤፌ 5፥25፤ ሉቃስ 16፥10።ላይ እንደምንመለከተው የመንግሥቱ ፍቅር በስሜት ብቻ የሚኖር ሳይሆን፣ በታማኝነትና በቁርጠ ኝነት የሚጸና ፍቅር ነውና።

**3 የእውነተኛ ፍቅር ዋጋ በገንዘብ ሊገዛ አይችልም**

መኃልየ መኃልይ 8፥7 **“ብዙ ውኃ ፍቅርን ሊያጠፋ አይችልም፥ ወንዞችም ሊያጥለቀልቁ ት አይችሉም።”** ይህ ጥቅስ እውነተኛ ፍቅር በችግርና በመከራ መካከል ያለውን ጽናት ይገ ልጻል። በተጨማሪም ፍቅር እንደ ሸቀጥ በገንዘብ ሊገዛ እንደማይችል ያስተምራል። በዓለ ም ውስጥ ሰዎች ገንዘብን፣ ሥልጣንንና ውጫዊ ውበትን ከፍ አድርገው ሊመለከቱ ይችላሉ ። ነገር ግን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሰው ዋጋ በገንዘቡ ወይም በማኅበራዊ ደረ ጃው አይለካም።በእግዚአብሔር መንግስት
ውስጥ **ፍቅር በገንዘብ ሳይሆን በቅንነት፣ በመስጠትና በታማኝነት ይገለጣል**። ይህ ማለት በትዳር ውስጥም ሆነ ከሌሎች ጋር ባለን ግንኝነት ችግር ፈጽሞ አይኖርም ማለት አይደለም። ይልቁንም በችግር ጊዜ **መግባባትን፣ ይ**

**ቅርታን፣ ትዕግሥትንና ታማኝነትን መለማመድ እንዳለብን ያሳስበናል**። ሆኖም ፍቅር ማ ለት በደልን መቀበል ወይም አደገኛ ሁኔታን በዝምታ መታገስ አይደለም።

**ግብረ**

**መልስ** ግንኙነታችንን በገንዘብ ብቻ አንለካ። በችግር ጊዜ በትዕግሥትና በጥበብ መፍትሔ እንፈልግ። ይቅርታንና መግባባትን እንለማመድ። በቤተሰባችንና በጉባኤህ ውስጥ ፍቅርን በተግባር እንግለጽ።1ኛ ቆሮ 13፥7።ምክንያቱም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እውነ ተኛ ፍቅር በገንዘብ አይገዛም፤ በችግር ጊዜም በጥበብ፣ በታማኝነትና በቁርጠኝነት መገለጥ አለበት።

**ማጠቃለያ** :- መኃልየ መኃልይ ስለ ፍቅር የሚያስተምረን መጽሐፍ ነው። ከእግዚአብሔር መ ንግሥት አንጻር ስናየውም ፍቅር በሕይወታችን፣ በትዳራችንና በግንኙነቶቻችን ውስጥ እንዴት መገለጥ እንዳለበት ከዚሁ መጻሐፍ እንማራለን።ከዚህ እውነት አንጻር ዛሬ ያየናቸው ሦስት ዋና ነጥቦች **ፍቅር የከበረ ስጦታ ነው። እውነተኛ ፍቅር ታማኝነ ትንና ቁርጠኝነትን ይጠይቃል። የእውነተኛ ፍቅር ዋጋ በገንዘብ ሊገዛ አይችልም**።የሚለውን ነው። እነዚህን መርሆች በቤተሰባችን፣ በትዳራችን፣ በቤተ ክርስቲያናችንና በማኅበረሰባችን ው ስጥ ስንተገብር፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እሴቶች በሕይወታችን ይገለጣሉ።ስለዚህ በቤተሰ ባችን ውስጥ የመንግሥቱን ፍቅር እንዴት ማሳየት እንችላለን?በችግር ጊዜ ታማኝነታችንን እን ዴት ልንጠብቅ እንችላለን?በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህንን የፍቅር ባሕል እንዴት ማሳደግ እን ችላለን? ብለን ዘወትር መጠይቅ አለብን **ፍቅር፣ ታማኝነትና የመንግሥቱ ባሕል ነውና**።